CITY OF ALEXANDRIA
VIRGINIA

# እንደገና ጥቅም ላይ መዋያ፣ የግቢ ውስጥ ቆሻሻ፣ እና የቆሻሻ መሰብሰቢያ አገልግሎቶች የ 2023 መመሪያ

DEPARTMENT OF TRANSPORTATION & ENVIRONMENTAL SERVICES

# በውስጡ ምን እንደያዘ


**የከተማውን የቆሻሻ ማንሳት አገልግሎት ለሚያገኙ ነዋሪዎች**

ሳምንታዊ የቆሻሻ መሰብሰብ አገልግሎት ገጽ 04
እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል ገጽ 06
የግቢ ውስጥ ቆሻሻና ሌሎች ቅሪቶች/ብስባሾች ገጽ 12
ቆሻሻ ገጽ 16

**ለሁሉም የከተማው ነዋሪዎች** — አገልግሎቶቹ ለሁሉም የከተማው ነዋሪዎች ይቀርባሉ

እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ ማስረከቢያ ማዕከላት ገጽ 08
ብርጭቆ ገጽ 09
በልዩ ዝግጅቶች ላይ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል ገጽ 10
የምግብ ቆሻሻ ብስባሽ ገጽ 15
የቆሻሻ ማስረከቢያ ማዕከል ገጽ 17
የቤተሰብ አደገኛ ቆሻሻ እና የኤሌክትሪክ እቃዎችን እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ማዕከል ገጽ 18
ባትሪዎች ገጽ 20
የመቀነሻና እንደገና መጠቀሚያ ፍንጮች ገጽ 21
የፕላስቲክ ከረጢቶችን ይቀንሱ ገጽ 22
የምግብ ቆሻሻን መቀነስ ገጽ 23
የበዓል ቆሻሻን መቀነስ ገጽ 24
የኦንላይን የመቀነሻ፣ መልሶ መጠቀሚያና እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ መሳሪያዎች ገጽ 25
እኛን እንዴት እንደሚያነጋግሩን ገጽ 27




# ስለ ሀብትን መልሶ ማግኛ ክፍል በተመለከተ



የከተማው ሀብትን መልሶ ማግኛ ክፍል/ Resource Recovery Division/ ሰራተኞች እና ተቋራጮች የማህበረሰባችንን ለኑሮ አመቺነት፣ አረንጓዴነትና ብልጽግና ለማስቀጠል በቀን ለ24 ሰዓቶችና በሳምንት ለሰባት ቀናት የሚሰራው የትልቅ ቡድን አካል ናቸው። እባክዎ በመቀነስ፣ መልሶ መጠቀም እና እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል አማካኝነት የቆሻሻ አያያዝ ተዋረድን በመከተል ከተማውን በዘላቂነት ሀብቶቹን እንዲያስመልስ ይርዱ! ተጨማሪ ለማወቅ alexandriava.gov/ResourceRecoveryን ይጎብኙ።

## ትርጉሞች

የዚህን መመሪያ የስፓኒሽ ወይም አማርኛ ቅጂ ለማግኘት እባክዎ የሚከተለውን ይጎብኙ:
alexandriava.gov/ResourceRecovery

Para leer esta guía en español, visite nuestro sitio web o use su teléfono para escanear el código QR.

ይህንን መመሪያ በአማርኛ ለማንበብ እባክዎን ድረገፃችንን ይጎብኙ ወይም ስልክዎን በመጠቀም የQR ኮዱን ስካን ያድርጉ።

**የቆሻሻ አያያዝ ተዋረድ**




የዩ.ኤስ የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ
የቆሻሻ አያያዝ ተዋረድ

# ሳምንታዊ የቆሻሻ መሰብሰብ አገልግሎቶች

## ብቁ የሆነው ማን እንደሆነ

የአሌክሳንደሪያ ለብቻቸው በተሰሩ፣ የአንድ ቤተሰብ፣ የሁለት ቤተሰብ መኖሪያ ቤቶች እና አንዳንድ አራት ወይም ከዚያ በታች ክፍሎች ያሏቸው የከተማዋ መኖሪያ ቤቶች ነዋሪዎች የዚህ ክፍያን መሰረት ያደረገ አገልግሎት ተፈላጊ ተጠቃሚዎች ናቸው። የንግድ ንብረቶችና የጋራ መኖሪያ ቤት ህንጻዎች ተፈላጊ ተጠቃሚዎች አይደሉም፣ ሆኖም በከተማዋ ውሳኔ በክፍያ ተሳታፊ ሊደረጉ ይችላሉ።

## እንዴት፣ መቼ፣ የት

### *ቆሻሻዬን ለስብሰባ እንዴት ማዘጋጀት እችላለሁ?*

- **እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ቆሻሻዎች** በከተማው በሚቀርብ **ልል** እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ቆሻሻዎች መያዣ ውስጥ መጨመር አለባቸው። ** ምንም የፕላስቲክ ከረጢቶች ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም።*
- የግቢ ውስጥ ቆሻሻዎች በደንበኛ በሚቀርብ ድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውል ጥብቅ የቆሻሻ መያዣ ወይም የወረቀት የግቢ ውስጥ ቆሻሻ መያዣ (ከምግብ/መጠጥ መደብር እና የሀርድ ዌር መደብሮች የሚገዛ) ውስጥ መጨመር አለባቸው።
- ቆሻሻ በከረጢት ውስጥ መጨመር እና በከተማው በሚቀርበው የቆሻሻ መያዣ ውስጥ መጨመር አለበት።

### *ቆሻሻዬን ለስብሰባ/ማንሳት ከቤት ማውጣት ያለብኝ መቼ ነው?*

ለእያንዳንዱ ደንበኛ በከተማው ውስጥ እንደሚኖርበት ቦታ ላይ ተመስርቶ የመሰብሰቢያ/ማንሻ ቀን ይመደብለታል። የመሰብሰቢያ/ማንሻ ቀንዎን ለማወቅ Alex311 ን ያነጋግሩ ወይም alexandriava.gov/RefuseCollectionን ይጎብኙ። ቆሻሻ፣ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ እና የግቢ ውስጥ ቆሻሻ ከቆሻሻ መሰብሰቢያ ቀኑ በፊት ባለው ቀን ከ 5 p.m. ሰዓት በፊት አለመውጣት እና በስብሰባው ቀን እስከ ጠዋት 6 a.m. ሰዓት መውጣት አለበት። የቆሻሻ ስብሰባ ቡድን አባላት ቆሻሻ መሰብሰቡ በ 6 a.m. ሰዓት ከሚጀምርበት የበጋው ወቅት በስተቀር ከሰኞ-አርብ፣ ከ 7 a.m.-5 p.m. ሰዓት ይሰራሉ። በዓልን በሚይዙ ሳምንታት ውስጥ የቆሻሻ መሰብሰቢያ ቀንዎ ከበዓሉ ቀጥሎ ያለው ቀን ይሆናል።

### *ቆሻሻዬን ለማሰብሰብ/ማንሳት የት ማስቀመጥ አለብኝ?*

ምንም እንኳን ለአንዳንድ ነዋሪዎች ቆሻሻው ከጠባብ መንገድ ላይ የሚወሰድ ቢሆንም ለአብዛኞቹ ለዋሪዎች ቆሻሻው ከመኖሪያ ቤት ፊት ለፊት ከሚገኝ የህዝብ መተላለፊያ መንገድ የቀኝ ጎን ላይ ይወሰዳል። ቆሻሻዎን ለስብሰባ/ማንሳት የት ማስቀመጥ እንዳለብዎ በተመለከተ እርግጠኛ ካልሆኑ Alex311 ን ያነጋግሩ። የቆሻሻ መሰብሰቢያ ኮንቴነሮች በአገልግሎት ቀንዎ እስከ 7 p.m. ሰዓት ድረስ ከህዝብ መኖሪያ ቤቶች ይወጣሉ።






## ቆሻሻዬ ሳይሰበሰብ አምልጦኛል!

የእርስዎ የሚጣሉትን ቁሳቁሶች ለስብሰባ ማዘጋጀት ለእኛ የቆሻሻ ምንጮችን መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል፣ ደህንነቱ የተጠበቀ ስብሰባን ለማረጋገጥ እና ቦታውን በጸዳና ንጹህ አኳኋን ለመያዝ እጅግ ወሳኝ ነው። የሚጣሉት ቁሳቁሶችዎ በቀኑ መጨረሻ ላይ የማይሰበሰቡ ከሆነ በከተማው ለምን እንዳልተሰበሰበ ከሚገልጸው ታግ ላይ ያረጋግጡ።

## የተለመዱ ችግሮች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ



- የመሰብሰቢያ ኮንቴነር፣ ከረጢት ወይም እቃው በጣም ከባድ መሆን።
- ከ 4 ጫማ በላይ ርዝመት ያላቸው እንደ ምንጣፍ እና ጣውላ የመሳሰሉ ቁሳቁሶች መሆን።
- የመያዣው እንደ የግንባታ ቁርጥራጮች፣ አቧራ፣ ጡብና ድንጋይ የመሳሰሉ ተቀባይነት የሌላቸው ቁሳቁሶች መያዝ (ነዋሪዎች ለእነዚህ ቁሳቁሶች የግል ጭኖ አስወጋጅ መጥራት አለባቸው)።
- እንደ ቤንዚን እና ያልደረቀ ቀለም የመሳሰሉ አደገኛ ወይም ብክለት ፈጣሪ ቁሳቁሶች።
- እንደገና ጥቅም ላይ ከሚውል ቆሻሻ ጋር የተቀላቀለ ቆሻሻ

**ታግ ከሌለስ?** ከ Alex311 ላይ “ሳይሰበሰብ ያመለጠ ስብስብ” ቲኬት ይጠይቁ

# ሳምንታዊ የቆሻሻ መሰብሰብ አገልግሎቶች

በ alex311 አማካኝነት አገልግሎቶችን መጠየቅ - ገጽ 27 ን ይመልከቱ።

## እርዱኝ፣ ቆሻሻዬን ወይም እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻዬን ማውጣት አልችልም

ቆሻሻዎን ወይም እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻዎን ወደ መንገድ ጠርዝ ወይም ጠባብ መንገድ መውሰድ ካልቻሉ አገልግሎት ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። የሚፈቀድልዎ ከሆነ ሰራተኞች ቆሻሻዎን ወይም እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻዎን ከመኖሪያ ቤትዎ ውጭ ከእርስዎ አመቺ በሆነ ቦታ ከሚቀመጠው የቆሻሻ ኮንቴነር ውስጥ ገልብጠው ሊወስዱ ይችላሉ። ማመልከቻ ለማግኘት ለ Alex311 ይደውሉ። ይህ አገልግሎት ለግቢ ውስጥ ቆሻሻ አይቀርብም።


## እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ ጋሪዎች ስፋት

የቆሻሻ መጣያ ጋሪዎች ስፋታቸው አንድ አይነት (65 ጋሎን) ቢሆንም እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ ጋሪዎች ሶስት የተለያዩ ስፋቶች አሏቸው።

እባክዎ ማመሳከሪያ መረጃ ለማግኘት ምስሉን ይመልከቱ።

1. 65 ጋሎን (የተመከረ)
2. 35 ጋሎን
3. 18 ጋሎን የቆሻሻ




*ሳምንታዊ የቆሻሻ መሰብሰብ ካርታ*

### የነዋሪዎች የመርሳት ክፍያ

ዓመታዊ የነዋሪዎች የቆሻሻ ማንሻ ክፍያዎ ሳምንታዊ የቆሻሻና እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ መሰብሰቢያን፣ የግቢ ውስጥ ቆሻሻ/ፍቅፋቂ መሰብሰቢያን፣ የቤተሰብ አደገኛ ቆሻሻ ማዕከል ስራዎችን፣ ልዩ ስብሰባዎችን (ቅጠል መሰብሰቢያን) እና የተሻሻሉ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ ፕሮግራሞችን ያጠቃልላል። ክፍያው በሪል ስቴት የግብር ክፍያዎ ላይ የተዘረዘረ ሲሆን በየግማሽ አመት ይከፈላል። ለንስነሳ አቅርቦት ወይም ከባድ ብረት/ የማብሰያ እቃዎች ማንሻ ተጨማሪ ክፍያዎች ሊጠየቁ ይችላሉ።

# እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል

እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል እቃ ገበያዎች በተከታታይ እየተቀየሩ ነው። እነዚህ ገበያዎች የሚቀያየሩ እንደመሆኑ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶችም ይቀያየራሉ። የመለያ ቴክኖሎጂዎች እና የማሸጊያ ዲዛይኖችም በጊዜ ሂደት የሚቀየሩ በመሆኑ ከተማው እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ፕሮግራሞቹን መርምሮ ማስተካከል ያስፈልገዋል። ከተማው ለእርስዎ ምን እንደገና ጥቅም ላይ እንደሚውልና ምን እንደገና ጥቅም ላይ እንደማይውል መረጃ በመስጠቱ ይቀጥላል።

### እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ በሰማያዊው ኮንቴነር ውስጥ የማይከተቱ ቁሳቁሶች ምን ይደረጋሉ?

የከተማውን እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ መሰብሰብ አገልግሎት የሚያገኙ ነዋሪዎች ለከባድ የብረት እቃዎች የማንሻ ቀጠሮ ሊያስይዙ ይችላሉ። ከብረት የተሰሩ የቤት ውስጥ የማብሰያ ዕቃዎች እና እንደ ከቤት ውጭ የሚያገለግሉ መጥበሻዎች፣ የአካል ብቃት መስሪያ መሳሪያዎች እና የአጥር ሽቦዎች የመሳሰሉ ትላልቅ የብረት ቁሳቁሶች በጥያቄ ወደ ምርትነት ሊቀየሩ ይችላሉ (ክፍያዎች ይከፈላሉ)።

የአገልግሎት ጥያቄ ለማስመዝገብ Alex311 ን ያነጋግሩ።

## በሰማያዊው ኮንቴነር ውስጥ ምን እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል መክተት አለብኝ?



ወረቀትና ካርቶን
ባዶ

ፕላስቲኮች
ባዶና የታጠቡ ተቀባይነት አላቸው

ብረቶች
ባዶና የታጠቡ ተቀባይነት አላቸው

የሚከተሉትን እንደገና ጥቅም ላይ አይውሉም!

ምንም ስፖንጅ አንቀበልም
ምንም ብርጭቆ አንቀበልም
ምንም የፕላስቲክ ከረጢቶች አንቀበልም
ምንም ባትሪዎችና የኤሌክትሪክ እቃዎች አንቀበልም
ምንም ልብሶች ወይም ጨርቃ ጨርቆች አንቀበልም
ምንም ጥልፎች (ገመዶች፣ ሹራቦች፣ ሽቦዎች) አንቀበልም።
ምንም የተተለተለ ወረቀት አንቀበልም
ምንም የቤት እንስሳት አይነ ምድር / ምንም ዳይፐሮች አንቀበልም
ምንም የህክምና ተረፈ ምርት / ስለት ነገሮች አንቀበልም

## እንደገና ጥቅም ላይ መዋያ መመሪዎች

1. ቁሳቁሶቹ ንጹህ፣ ባዶና ደረቅ መሆን አለባቸው። አስፈላጊ ከሆነ ይጠቧቸው። ምንም የምግብ ትራፊ መኖር የለበትም።
2. የእቃ መያዣዎቹን ባዶ ካደረጓቸው በኋላ ክዳናቸውን መልሰው ይክደኑ።
3. ከ 3 x 3 ኢንች ያነሱ ቁሳቁሶች እንደገና ጥቅም ላይ ከማዋያ መሳሪያው ይሾልካሉ። ምንም የማብሰያ እቃዎችና መምጠጫዎች መኖር የለባቸውም።
4. ካርቶኑን አራግፈው ይዘረጋጉት። ከካርቶኑ ውስጥ አየር መሙያዎች፣ ስፖንጅ ወይም የፕላስቲክ መጠቅለያ ያውጡ።
5. የፕላስቲክ ቁጥሮች (#1-7) እንደገና ጥቅም ላይ መዋልን አይወስኑም። አንገታቸው ከ #1 እና #2 የተሰሩ ጠንካራ የፕላስቲክ መያዣዎች እና ፕላስቲኮች በክልሉ ውስጥ በስፋት እንደገና ጥቅም ላይ ይውላሉ።
6. የፕላስቲክ ኩባያዎች፣ ትሪዎች እና እንደ ይዞ መሄጃ መያዣዎች ወይም የፕላስቲክ የፍራፍሬ መያዣዎች የመሳሰሉ መያዣዎችን እንደገና ጥቅም ላይ አያውሉ። ምንም እንኳ ሁሉም ፕላስቲኮች እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ ቢችሉም ገበያው የትኞቹ የፕላስቲክ አይነቶች ወደ ምርትነት እንደሚቀየሩ ይመራናል።
7. ለአንሳይን እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ መሳሪያዎች ለቅርብ የአዎ/አይ ዝርዝር alexandriava.gov/Recyclingን ይጎብኙ።





## ምንም የፕላስቲክ ከረጢቶች እንደገና ጥቅም ላይ አይውሉም!

ምንም የፕላስቲክ ከረጢቶች፣ መጠቅለያዎች፣ እና የትኛውም ቀለም፣ መጠን ወይም ቅርጽ ያላቸው ፊልሞች በከተማው እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ ቅርጫት ተቀባይነት የላቸውም። የፕላስቲክ ከረጢቶች በአብዛኛው በከተማው እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ መስመር ውስጥ ትልቁን ቦታ ይይዛሉ።

እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ተቋማት በአብዛኛው እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ እቃዎችን የፕላስቲክ የቆሻሻ ከረጢት ወይም የትኛውንም አይነት መጠቅለያዎች እና ፊልሞች የሚይዙ ከሆነ እነዚህን አይቀበሉም። በተጨማሪም ከተማዋ ከረጢቶችና መጠቅለያዎቹ የሚገኙ ከሆነ ቅጣት ትከፍላለች። እባክዎ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ቆሻሻዎችዎን ብትን በማድረግ የከተማዋን የብክለት ቅነሳ ይርዱ።



ሰራተኞች ጥልፍልፍ የፕላስቲክ ከረጢቶችን እንደገና ጥቅም ላይ ከማዋያ መሳሪያው ውስጥ ያስወግዳሉ።

### የፕላስቲክ ከረጢት ማስረከቢያ ቦታ

የፕላስቲክ ከረጢቶች፣ መጠቅለያዎች እና ፊልሞች በተሳታፊ የምግብ/መጠጥ መደብሮች እና የችርቻሮ መሸጫዎች የሚቀመጡ ከሆነ እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።

## እንደገና ጥቅም ላይ የማወል መብት አሌክሳንደሪያ

### ምንም የፕላስቲክ ከረጢቶች

## የሚከተለውን አያድርጉ ከረጢት እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ እቃዎች



**የፕላስቲክ ከረጢቶችን ለችርቻሮ መሸጫዎች ይመልሱ።**

በቅርብዎ የሚገኝ ችርቻሮ ሻጭ ይፈልጉ: plasticfilmrecycling.org

# እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ ማስረከቢያ ማዕከላት

## በማስረከቢያ ማእከላት የሚካሄድ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል


እንደገና ጥቅም ላይ ለማዋል መጠበቅ አየቻሉም? ከተማው ለሁሉም የከተማው ነዋሪዎች እና አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች አራት የህዝብ የቆሻሻ ማስረከቢያ ማዕከላት ያቀርባል።

- **4251 Eisenhower Ave.**
- **3224 Colvin St.**
- **S. Royal St. and Jones Point Dr.**
- **Tower Ct. South Whiting St.**

በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት ሰባት ቀናት

ነጻ

alexandria.gov/go/2768




**ተቀባይነት ያላቸው ቁሳቁሶች:**
- ቅይጥ የእቃ መያዣዎች (የአልሙኒየም ድስቶች፣ የብረት ድስቶች፣ የፕላስቲክ ጠርሙሶች እና ጀጎች)
- ቅይጥ ወረቀት
- ባዶ ተደርጎ የተዘረጋጋ ካርቶን (ከውስጡ ስፖንጅና የፕላስቲክ መጠቅለያዎች ያስወግዱ)

**ተቀባይነት የሌላቸው ቁሳቁሶች:-**
- ምንም ብርጭቆ ተቀባይነት የለውም (በምርተነት መቀየሪያ ማዕከላት በጣምራ የተቀመጡትን ሀምራዊ ቀለም ቅርጫቶች ይጠቀሙ)
- ምንም ስፖንጅ ወይም የኦቾሎኒ ማሸጊያዎች ተቀባይነት የላቸውም።
- ምንም ድስቶችና መጥበሻዎች ተቀባይነት የላቸውም።
- ምንም የፕላስቲክ ከረጢቶች፣ መጠቅለያዎች ወይም ፊልም ተቀባይነት የላቸውም።
- ምንም ቆሻሻ፣ ፈርኒቸር፣ ብትን ቆሻሻ ወይም የግቢ ውስጥ ቆሻሻ ተቀባይነት የለውም **(ህገወጥ ቆሻሻ መጣል የተከለከለ ነው)**



## ህገወጥ ቆሻሻ መጣልን እንድንታገል ይርዱን

ህገወጥ ቆሻሻ መጣል ቆሻሻ በህገወጥ መንገድ ማስወገድ ነው። ህገወጥ ቆሻሻ መጣል እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ማእከላትን በመድፈን ለችግር ያጋልጣቸዋል። ማንኛውንም በሂደት ላይ ያሉ ጥሰቶችን ማየት አለብኝ? ህገወጥ ቆሻሻ መጣልን Alex311ን በማነጋገር ለከተማው ሪፖርት ያድርጉ።

ህገወጥ ቆሻሻ መጣልን ማስቆም አካባቢን ጥሩ በማድረግ የኢኮኖሚ ስሜት የሚፈጥር ከመሆኑም በተጨማሪ የሁሉም ሰው ጉዳይ ነው። ለንጹህ፣ ጤናማና አስተማማኝ/ደህንነቱ የተጠበቀ ማህበረሰብ ከአካባቢዎ የህግ አስፈጻሚ ባለስልጣናት ጋር አብረው በመስራት ይህን ችግር እንድንቀርፍ ይርዱን።

የአሌክሳንደሪያ ከተማ የህዝብ ችግር ፈጣሪን በመዋጋት ላይ ጥብቅ ነው። የራስዎን ድርሻ በመወጣት የማህበረሰባችንን ንጽህናና ጤናማነት እንድንጠብቅ ይርዱን።





# ብርጭቆ



**አዎ!**

- ባዶና የታጠቡ
- ምልክቶች - ተቀባይነት አላቸው
- ሁሉም የብርጭቆ ቀለሞች - ተቀባይነት አላቸው
- የብረት ክዳኖችና ሊዶች - ተቀባይነት አላቸው

**ተቀባይነት የላቸውም!**

- ብርጭቆ ከረጢት ውስጥ አይክተቱ ምንም የፕላስቲክ ጥቅሎች ተቀባይነት የላቸውም
- ምንም የፕላስቲክ ከረጢቶች ወይም የፕላስቲክ ጥቅል (ለችርቻሮ ሻጩ ይመልሱ)
- ምንም መብራቶች ወይም አምፑሎች ተቀባይነት የላቸውም (በ 3224 Colvin St. የሚገኘውን የቤተሰብ የአደገኛ ቆሻሻ ማስወገጃ ማዕከልን ይጠቀሙ)
- ምንም ብርጭቆ፣ ሴራሚክስ፣ ፖርሲሊን መስታወቶች፣ መስኮቶች ፕሬክስ፣ ወይም ልሙጥ መስታወት
- ምንም ምግብ ወይም ፈሳሽ (ባዶ ያድርጉና ይጠቡ)



**ምንም ብርጭቆ በሰማያዊው ኮንቴነር ውስጥ መከተት የለባቸውም እንደገና ጥቅም ላይ ይውላል!**

ብርጭቆ ከዚህ በኋላ በመንገድ ዳር እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ፕሮግራም ተቀባይነት የለውም።

## ነዋሪዎች ሁለት አማራጮች አሏቸው:-

በሀምራዊ የብርጭቆ ብቻ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ቅርጫቶች ውስጥ መክተት። ብርጭቆዎችን በመንገድ ዳር የቆሻሻ ጋሪዎች ውስጥ መጨመር።

በሀምራዊ የብርጭቆ ብቻ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ቅርጫቶች ውስጥ የሚከተት ብርጭቆ ለአካባቢው የህዝብ ስራዎች ፕሮጀክቶች ወደሚያገለግሉ አዲስ የብርጭቆ ጠርሙሶችና ቁሳቁሶች ይቀየራል።

alexandria.gov/go/2771


## የብርጭቆ መክተቻ ቦታዎች

- **4251 Eisenhower Ave.**
- **3224 Colvin St.**
- **S. Royal St. and Jones Point Dr.**
- **Tower Ct. and South Whiting St.**
- **3831 Mt. Vernon Ave.**

በሰሜን ቨርጂኒያ ውስጥ ለሚገኙ ተጨማሪ ቦታዎች alexandria.gov/go/2771ን ይጎብኙ።

በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት ሰባት ቀናት

ነጻ



# በልዩ ዝግጅቶች ላይ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል

## በዝግጅትዎ ላይ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል

እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል በዝግጅትዎ ላይ የሚፈጠረውን ቆሻሻ መጠን ለመቀነስ አንዱ ቀላልና ርካሽ ዘዴ ነው። እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል በአራት ቀላል መንገዶች ሊዘጋጅ ይችላል።




1. በዝግጅትዎ ላይ እንደገና ጥቅም ላይ ለማዋል ይወስኑ እና አስ ተባባሪ በተለይም ለትላልቅ ዝግጅቶች ያዘጋጁ።
2. የመሰብሰቢያ ስርአት ያቅዱና ያዘጋጁ።

- ምን አይነት ቆሻሻና ምን አይነት እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ኮንቴነሮች ይጠቀማሉ?
- ምን ያክል ቆሻሻና ምን አይነት እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ኮንቴነሮች ይጠቀማሉ?
- የአውራ ጣት ሕግ ለእያንዳንዱ የቆሻሻ ቅርጫት አንድ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ኮንቴነር መጠቀም ነው።
- ቆሻሻውና እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ኮንቴነሩ የት ይቀመጣሉ? ቆሻሻ ውን እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ኮንቴነሩን በከፍተኛ ደረጃ በሚታዩና በቀላሉ ሊደረሱ በሚችሉ ቦታዎች አንዱን ከሌላኛው ቀጥሎ ያስቀምጡ።
- ቆሻሻውን እና እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ኮንቴነሩን የማራገፍ ኃላፊነት የማን ነው?
- ከዝግጅቱ ማብቃት በኋላ ቆሻሻውን እና እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያውን የሚ ያስወግደው ማን ነው? ጫኝ፣ ግለሰብ፣ ወዘተ። ለትናንሽ ዝግጅቶች የከተ ማው እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ቆሻሻዎችን ማስረከቢያ ቦታ አለ።

3. መሰረታዊ እንገና ጥቅም ላይ የማዋል ትምህርትን ያስተዋውቁ እንዲሁም ያስተምሩ።

- በዝግጅቱ መጀመሪያ ላይ እና በዝግጅቱ ወቅት ውስጥ በሙሉ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ እንዳለ ያስተዋውቁ።
- ምን እንደገና ጥቅም ላይ እንደሚውል የሚያሳዩ ምልክቶች ይለጥፉ።
- በቆሻሻና እንደና ጥቅም ላይ ማዋያ ኮንቴነሮች ላይ በአ ግባቡ ምልክት መደረጉን ያረጋግጡ።

4. በቆሻሻውና እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ኮንቴነ ሮቹ ላይ ማንኛውም ብክለት እንዳይፈጠር ይቆ ጣጠሩ (ማለትም እንደገና ጥቅም ላይ በዋያ ኮን ቴነሩ ውስጥ ያለው ቆሻሻና በተገላቢጦሹ)።

- በተለይም ለትላልቅ ዝግጅቶች ለዝግጅቱ መጪ እንግዶች ምን እንደገና ጥቅም ላይ እንደሚውልና ምን እንደገገና ጥቅም ላይ እንደማይውል፣ እንዲሁም እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሶች ወዴት እንደሚቀመጡ የሚያስታውሱ በጎ ፍቃደኞች ያዘጋጁ።

**ለልዩ ዝግጅትዎ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ኮንቴነሮች ይፈልጋሉ?**
የአሌክሳንደሪያ ከተማ ንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ፕሮግራም በከ ተማው ውስጥ ለሚዘጋጁ ዝግጅቶች ሊከራዩ የሚችሉ 47 እንደ ገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶችን መቀበያ ኮንቴነሮች አሉት። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ከታች ድረገጻችንን ይጎብኙ።

alexandriava.gov/go/2723






# በህዝብ መሰባሰቢያ ቦታ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል

## በጉዞ ላይ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል

እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ኮንቴነሮች እንደ King Street እና Mount Vernon Ave. በመሳሰሉ የተለመዱ የእግረኛ መንገዶች ላይ እና በከተማው ፓርኮች ውስጥ ይቀመጣሉ።




**ተቀባይነት ያላቸው ቁሳቁሶች:**

- የፕላስቲክ ጠርሙሶች
- የአልሙኒየም ድስቶች
- ቅይጥ ወረቀት

**ተቀባይነት የሌላቸው ቁሳቁሶች:**

- ብርጭቆ (ሐምራዊውን ቅርጫት በመጠቀም እንደገና ጥቅም ላይ ያውሉት ወይም በቆሻሻ መጣያ ውስጥ ያስወግዱት)
- የቤት እንስሳት አይነ ምድር
- ስፖንጅ
- የፕላስቲክ ከረጢት/ፊልም/መጠቅለያ
- ግዙፍ ቆሻሻ
- የምግብ መያዣዎች (ለምሳሌ:- ይዞ መሄጃ መያዣዎች፣ ኩባያዎች ወይም ትሪዎች)፣ ወይም ሌላ ቆሻሻ

**እባክዎ እንደ ካርቶን ወይም ትላልቅ የፕላስቲክ ጆጎች የመሳሰሉ ግዙፍ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ቆሻሻዎችን ወደ ከተማው እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ቆሻሻዎችን ማስረከቢያ ማዕከል ይውሰዷቸው።*

alexandriava.gov/go/2723



## ስማያዊው ኮንቴነር ውስጥ ሰገራ አይጨመርም

በህዝብ መሰብሰቢያ ቦታ የሚገኙ ኮንቴነሮች ተጠቃሚዎች የእንስሳቶቻቸውን አይነ ምድር በሰማያዊው እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ኮንቴነር ውስጥ ከመክተት መታቀብ እና ለእንስሳት አይነ ምድር የተዘጋጁ የቆሻሻ ኮንቴነሮችን ብቻ መጠቀም አለባቸው።

የእንስሳት አይነ ምድር እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶችን ስለሚበክል ቆሻሻ ውስጥ እንድንጥላቸው ያስገድደናል።

# የግቢ ውስጥ ቆሻሻ



## የግቢ ውስጥ ቆሻሻ - መደበኛ መሰብሰብ/መረከብ

ሳር፣ ቅጠሎች፣ ቡርሾች፣ ቅርንጫፎችና የደረቁ ተክሎች እንደ ኦርጋኒክ ፍግ እና ገለባ የመሳሰሉ ጠቃሚ ምርቶችን ለማምረት የሚያገለግሉ ግብአቶች ናቸው። እነዚህ የቤት ውስጥ ቆሻሻ ተብለው የሚጠሩት ግብአቶች ከሌሎች የቤት ውስጥ ቆሻሻዎች ተለይተው ለብቻቸው ይሰበሰባሉ። ከተማው ይህን ቆሻሻ ፍግ ወይም ገለባ ለማምረት ታቀነባብራለች። ከተማው የግቢ ውስጥ ቆሻሻ ኮንቴነሮችን አያቀርብም/ አይጠግንም ወይም አይቀይርም። የቤት ውስጥ ቆሻሻዎችን በጠንካራ/ድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ መያዣዎች የወረቀት የቤት ውስጥ ቆሻሻ መያዣ ከረጢቶች (ከግሮሰሪ እና የሀርድዌር መደብሮች የሚገዙ) ውስጥ ይጨምሩ እና ቆሻሻ ማስቀመጫዎ ቀጥሎ ያስቀምጧቸው። ስብሰባው ከቆሻሻ መሰብሰቢያው ቀን ጋር በተመሳሳይ ቀን ይካሄዳል።

የግቢ ውስጥ ቆሻሻ - አዎ!

- ፍቅፋቂና ቅርንጫፎች
- ሳር
- ቅጠሎች
- የደረቁ ተክሎች




አይ!

- ❌ ቁጥቋጦዎች፣ አፈር፣ ጥልፍ፣ ሶዳ (በግል የማስወገድ አገልግሎት ለማግኘት ያመቻቹ)
- ❌ የቤት እንስሳት አይነ ምድር (ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ያስወግዱ)

alexandriava.gov/YardWaste

### ግዙፍ የግቢ ውስጥ ቆሻሻ - በጥያቄ

ኮንቴነሩ ውስጥ ለመግባት ከባድ ወይም ትልቅ የሆኑ ፍቅፋቂ፣ ቅርንጫፎች እና የእንጨት ቁራጮች በጥያቄ ከመንገድ ዳር ይሰበሰባሉ። ሰራተኞች በመንገድ ዳር እስከ ሁለት የወደቁ ዛፎችን ይሰበስባሉ (ገደቦች ተፈጻሚ ይደረጋሉ፣ ከታች ይመልከቱ)

የመሰብሰቢያ ቀን ቀጠሮ ለማስያዝ Alex311 ን ይጠቀሙ።

### ዝግጅት

- የሚሰበሰቡት ዲያሜትራቸው ከ18 ኢንች እና ቁመታቸው ከ 10 ጫማ በታች ለሆኑ የእንጨት ቁራጮችና ቅርንጫፎች ብቻ ናቸው። ምንም ጉቶዎች አይሰበሰቡም።
- **ፍቅፋቂ በቆሻሻ መጣያ ቦታ ወይም ጠባብ መንገድ ላይ ሳይሆን በመንገድ ዳር ያስቀምጡ።** ትላልቅ ቁሶችን በመንገድ ጠርዝ ትይዩ ያስቀምጡ።
- ወደ ላይ 25 ጫማ ክፍተት መፍጠር ያስፈልጋል (የሀይል መስመሮችና የዛፍ ቅርንጫፎችን ይመልከቱ)
- ጣውላ ወይም የግንባታ ቁርጥራጮችን ከፍቅፋቂ ጋር አይቀላቅሉ።
- ፍቅፋቂ ከቆመ መኪና አጠገብ አያስቀምጡ፤ 10 ጫማ ክፍተት መፍጠር ያስፈልጋል።
- ፍቅፋቂ እንደ ቋሚዎች፣ የመንገድ መብራቶች፣ አጥሮች፣ ግድግዳዎች ወይም ህንጻዎች ላይ አስደግፈው አያስቀምጡ።
- የእግረኛ መንገዶችን አይዝጉ

የግቢ ውስጥ ቆሻሻ ኮንቴነርዎን ለመለየት የሚያስችል **"የግቢ ውስጥ ቆሻሻ ብቻ"** ምልክት ለማግኘት **Alex311**ን ያነጋግሩ።



# ሌሎች ብስባሾች

## የገና ዛፎች

የከተማዋን የስብሰባ አገልግሎት የሚያገኙ ነዋሪዎች የተፈጥሮ የገና ዛፎችን በጥር ወር የመጀመሪያዎቹ ሙሉ ሁሉት ሳምንታት በመደበኛ የቆሻሻ መሰብሰቢያ ቀናት ውስጥ በመንገድ ጠርዝ ላይ ሊያስቀምጡ ይችላሉ። ዛፎቹ የበሰበሱ የጥድ ቅጠሎች ሆነው መሬት ላይ ይወድቃሉ። ቋሚዎች፣ ብልጭልጮች፣ ማስዋቢያዎች እና መብራቶች መወገድ አለባቸው።

## የጸደይ ወቅት ቅጠልና የእንጨት ብስባሽ



በፀደይና የበጋ ወቅት ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ በከተማዋ የብስባሽ መሰብሰቢያ ቦታ (4251 Eisenhower Ave.) ቀድሞ የመጣ ቀድሞ ይስተናገዳል በሚለው መርህ ላይ ተመስርቶ ብስባሽ በነጻ ይቀርባል።

ቦታው ከ Eisenhower Ave. ጋር በጥምረት ይገኛል። እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ማዕከል።

በፀደይ ወቅትና በበጋ ወቅት የመጀመሪያዎቹ ወራት ውስጥ የብስባሽ አቅርቦት ቀጠሮ ለማስያዝ ለ Alex311 ሊደውሉ ወይም ከታች የተገለጸውን ድረገጻችንን ሊጎበኙ ይችላሉ። አቅርቦቱ ለእያንዳንዱ ግማሽ ጭጭት $65 እና ለሙሉ ጭነት $130 ያስከፍላል። ለአቅርቦቶቹ በእረፍት ወይም የበአል ቀናት ሳይሆን ከሰኞ-አርብ ቀጠሮ ይያዛል።

alexandriava.gov/YardWaste

## አዲስ! የመንገድ ዳር የምግብ ቆሻሻን/ተረፈ ምርትን ወደ ማዳበሪያነት የመቀየር ሙከራ 2023-2025

የአሌክሳንደሪያ ከተማ የከተማውን የቆሻሻና እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ ማንሳት አገልግሎት ለሚያገኙ ነዋሪዎች አዲስ የመንገድ ዳር የምግብ ቆሻሻን ወደ ማዳበሪያነት የመቀየር ፕሮግራም ተግባራዊ አድርጓል። ለሙከራ ፕሮግራሙ የተፈቀደላቸው ነዋሪዎች እንደ የፍራፍሬና አትክልት፣ ስጋና አጥንት የመሳሰሉ ተረፈ ምርቶችን ቆሻሻ መጣያ ቦታ ከመጣል ይልቅ ለምግብ ቆሻሻ መሰብሰቢያ በተመደበው ቅርጫት ውስጥ መክተት ይችላሉ።

ለሙከራ ፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ለመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት የአቅርቦትና ስብሰባ ወጪውን በገንዘብ ይደጉማሉ። ከስድስት ወራት በኋላ ነዋሪዎች በወርሀዊ ወይም ዓመታዊ የአገልግሎት ክፍያ አገልግሎቱን ከአቅራቢ ማግኘታቸውን ይቀጥላሉ። *ከተማው በአሁኑ ወቅት ከነዋሪዎች የቆሻሻ ማንሻ ክፍያ ነጻ ለተደረጉ እና የታክስ እፎይታና ድጎማ ለሚያገኙ ለ 100 ቤተሰቦች የአስራ ሁለት ወር ድጎማ ይሰጣል። ለሁለት ዓመታት በየዓመቱ እስከ 2,000 ቤተሰቦች ለሙከራ ፕሮግራሙ ይመረጣሉ። ስለ አገልግሎቱ በተመለከተ ተጨማሪ ለማወቅ እባክዎ ድረገጻችንን ይጎብኙ።


alexandriava.gov/go/4289



# ቅጠል መሰብሰብ

alexandriava.gov/LeafCollection


ከጥቅምት መጨረሻ አንስቶ እስከ ጥር ወር ድረስ የከተማው የቆሻሻ ስብሰባ ቡድኖች ቅጠል በንፋስ መሰብሰቢያ መኪናዎችን በማሰማራትየወረቀት የቅጠል ከረጢቶችን ይሰበስባሉ። ዓመታዊ የመንገድ ዳር ቅጠል ስብሰባ ፕሮግራሙ ለሁሉም የከተማው የነዋሪዎች የቆሻሻና እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ቆሻሻዎች ማንሳት አገልግሎቶችን ለሚያገኙ ነዋሪዎች ይቀርባል። አሌክሳንደሪያ እያንዳንዳቸው የራሳቸው መጀመሪያ ቀን እና ሶስት የተለያዩ ማለፊያዎች ባላቸው አምስት የመሰብሰቢያ ዞኖች የተከፋፈለ ነው። ነዋሪዎች በመኖሪያ ቤት አድራሻቸው ላይ ተመስርተው የተመደቡላቸውን የቅጠል መሰብሰቢያ ቀናት ለማየት የነዋሪዎች የቅጠል ስብሰባ ማሳያን (በከተማው የቅጠል ስብሰባ ድረገጽ ላይ የሚገኝ መረጃ ሰጪ ካርታ) ማየት ይችላሉ።




## ቅጠሎችዎን እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ሶስት መንገዶች

የከተማውን የቆሻሻና እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ ስብሰባ አገልግሎቶች የሚገኙ ነዋሪዎች ቅጠሎችን በሶስት መንገዶች እንደገና ጥቅም ላይ ሊያውሉ ይችላሉ።

### 1) ቅጠል በንፋስ ማጽዳት



ቅጠሎች በሚረግፉበት ወቅት የከተማው የቆሻሻ ስብሰባ ቡድኖች የመንገድ ዳር ቅጠሎችን በንፋስ መኪና አማካኝነት ይጠርጋሉ። የአየር ጠባዩ ከፈቀደ የከተማው ሰራተኞች በእያንዳንዱ ሰፈር ዞን ሶስት ማለፊያ ያዘጋጃሉ። ለስብሰባ ቡድኖቹ በእያንዳንዱ ዞን ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱን ማለፊያ ለማጠናቀቅ ከአንድ በላይ ቀን ይወስድባቸዋል።

*እንዴት እንደሚያዘጋጁ*

- ቅጠሎችን ከተመደበልዎ የመሰብሰቢያ ቀን በፊት ባለው ቀን ጠርገው ያከማቹ (ሳምንታዊ የተስተካከለ የጊዜ ሰሌዳን በኦንላይን ያረጋግጡ ወይም ሳምንታዊ የተስተካከሉ የጊዜ ሰሌዳዎችን ለማግኘት ለ T&ES' የሀብት ማስመለሻ ኢ-ዜናዎች ይመዝገቡ)።
- ቅጠሎች ጠርገው መንገድ ዳር ይከምሯቸው። ይህ ሰብሳቢ ቡድኖቹን በፍጥነትና ውጤታማነት እንዲያልፉ ይረዳቸዋል።
- ከቅጠሎቹ ላይ ጠጠሮችን፣ ቆሻሻ፣ ቅርንጫፎችን ወይም ሌሎች ቁርጥራጮችን ያስወግዱ። እነዚህ ካሉ መሳሪያውን ሊያበላሹትና በሰራተኞቻችን ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ።
- ቅጠሎቹን ከክፍት ቦይ ፊት ለፊት ወይም ከውሀ መስመር ክዳን አጠገብ አያስቀምጧቸው።
- የሚቆሙ መኪናዎችን ከተከመሩ ቅጠሎች ርቀው እንዲቆሙ ያድርጓቸው።
- ቅጠሎችን ወደ ጎዳናዎች ወይም የአገልግሎት መንገዶች አይጥረጉ። ጎዳናዎች ላይ የሚበታተኑ ቅጠሎች አይጠረጉም

### 2) የቅጠል ከረጢት ስብሰባ



በቅጠል መሰብሰቢያ ወቅት ውስጥ ከተማው እጁ ላይ ያለው አቅርቦት እስከሚያልቅ ድረስ መጀመሪያ የመጣ ቀድሞ ይስተናገዳል በሚለው መነሻነት ለቅጠል መሰብሰቢያ የሚበሰብሱ የወረቀት ከረጢቶችን ይሰጣል። ነዋሪዎች ከረጢቶቹን አንስቶ ለመሄድ በተለያዩ የከተማው ተቋማት ውስጥ የሚያገኟቸው ሲሆን ለንግድ ግልጋሎት አይቀርቡም። ከረጢቶቹ በመደበኛ የቆሻሻ መሰብሰቢያ ቀንዎ ቆሻሻዎ ከሚሰበሰብበት ቦታ (ቆሻሻዎን፣ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻዎንና የግቢ ውስጥ ቆሻሻዎን) ከሚያስቀምጡበት ቦታ ይሰበሰባሉ።

*እንዴት እንደሚያዘጋጁ*

- የወረቀት ከረጢቶቹን በመደበኛ የቆሻሻ መሰብሰቢያ ቀንዎ ቆሻሻዎ የሚሰበሰብበት ቦታ ላይ ያስቀምጧቸው። የወረቀት ከረጢቶችን ብቻ ይጠቀሙ። በፕላስቲክ ከረጢቶች ውስጥ የሚጨመሩ ቅጠሎች እንደማያገለግሉ ቆሻሻ ተቆጥረው ወደ Covanta Energy-from-Waste plant ይወረወራሉ።
- ቅጠሎችን ወደ ከረጢቶቹ ውስጥ ከመጨመርዎ በፊት ከላያቸው ላይ አቧራ፣ ቆሻሻና ሌሎች ቁርጥራጮችን ያንሱላቸው።

### 3) ቅጠሎችን በቤት ውስጥ ወደ ማዳበሪያነት መቀየር

ቅጠሎችን በቤት ውስጥ ወደ ማዳበሪያነት መቀየር አንዱ ቀላል የተፈጥሮ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ዘዴ ሲሆን ጠቃሚ ኦርጋኒክ ማዳበሪያዎችን ከመስጠት በተጨማሪ በቤትዎ ጓሮ ውስጥ በቀላሉ መሰራት ይችላል። ስለ ሳርን እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል፣ የግቢ ውስጥ ቆሻሻን ወደ ማዳበሪያነት መቀየር እና የከተማው የአርሷደሮች ገበያ የማዳበሪያ ጣቢያዎችን በተመለከተ ተጨማሪ ለማወቅ **alexandriava.gov/ResourceRecovery** ን ይጎብኙ።



# በአርሷደሮች ገበያ ላይ የምግብ ቆሻሻን ወደ ማዳበሪያነት መቀየር

ከምግብ ትርፍራፊዎች የሚሰራ ማዳበሪያ አፈርን በንጥረ ነገር ያበለጽጋል።

| ማዳበሪያ አዎ | ማዳበሪያ አይ |
| --- | --- |
| ለውዝ፣ ባቄላ፣ ዘሮች (ልጣጮች/ቅርፊቶችን ጨምሮ) | ዘይት |
| ፍራፍሬዎችና አትክልት ቁርጥራጮች | የፕላስቲክ ከረጢቶች |
| የተበላሸ ቡና፣ የቡና አተላ፣ የሻይ ቅጠል ካርቶኖች (ከላይ ወይም ከውስጥ በፎይል ያልተጠቀለሉ ምርቶች) | ስጋ፣ የባህር ምግብ እና አጥንት |
| ዳቦ፣ ፓስታ፣ ሩዝ እህሎችና ጥራጥሬዎች | የወተት ተዋጽኦዎች |
| የእንቁላል ቅርፊቶች | ናፕኪኖች፣ ሶፍት |
| አበባዎች | የቤት እንስሳት አይነ ምድር |




ምግቦችን በነጻ ወደ የበለጸገ የአፈር ማዳበሪያነት መቀየር እንዲችሉ በእረፍት ቀናት ወደ አርሷደሮች ገበያ ወስዶ ማስረከብ ይቻላል። ሰራተኞች ወደ ማዳበሪያነት ስለመቀየር የተመለከቱ ጥያቄዎችን ለመመለስና እንዴት የምግብ ቆሻሻን መቀነስ እንደሚቻል የተመለከተ ምክር ለመስጠት ዝግጁ ናቸው።

## የአሌክሳንደሪያ ከተማ የምግብ ቆሻሻ ወደ ማዳበሪያነት መቀየሪያ ቦታዎች የምግብ ተረፈ ምርቶችን አፈርን ወደሚያበለጽግ ማዳበሪያነት ይቀይራሉ።

### ቦታዎች

**ዴል ሬይ የአርሷደሮች ገበያ/ Del Ray Farmers' Market**
Corner of East Oxford & Mount Vernon Avenues
በየሳምንቱ እሁድ ከ 8 a.m. - 12 p.m. ሰዓት
ዓመቱን ሙሉ ክፍት ነው

**ኦልድ ታውን የአርሷደሮች ገበያ/ Old Town Farmers' Market**
Market Square, 301 King Street
በየሳምንቱ እሁድ ከ 8 a.m. - 12 p.m. ሰዓት
ዓመቱን ሙሉ ክፍት ነው

**ፎር ማይል ረን የአርሷደሮች ገበያ/Four Mile Run Farmers' Market**
4109 Mount Vernon Avenue
በየሳምንቱ እሁድ ከ 9 a.m. - 1 p.m.
ዓመቱን ሙሉ ክፍት ነው

**ዌስት ኢንድ የአርሷደሮች ገበያ/ West End Farmers' Market**
4800 Brenman Park Drive
በየሳምንቱ እሁድ ከ 8.30 a.m. - 1 p.m. ሰዓት
ወቅትን የተከተለ ገበያ - ቀናቱን ለማወቅ ድረገጽ ይመልከቱ

**ኦልድ ታውን ኖርዝ/ Old Town North**
የአርሷደሮች ገበያ/ Farmers Market
901 North Royal Street
በየሳምንቱ እሁድ ከ 10 a.m. - 2 p.m. ሰዓት
ዓመቱን ሙሉ ክፍት ነው

**ኒው ሳውዘርን ታወርስ/NEW Southern Towers**
የአርሷደሮች ገበያ/ Farmers Market
4901 Seminary Rd
በየሳምንቱ ቅዳሜ ከ 10 a.m. - 2 p.m. ሰዓት
ዓመቱን ሙሉ ክፍት ነው



## ምግብን ይቆጥቡ

### አሜሪካ ውስጥ ከሁሉም ምግቦች 40% ያክሉ ይባክናል።

የምግብ ብክነትን መበላሸት ከመጀመሩ በፊት ማቆም እና ምግቡን መለገስ ምግቡን ወደ ማዳበሪያነት ከመቀየር በፊት ተመራጭ አሰራር ነው። የምግብ ብክነትን ስለመከላከል፣ ምግብ የት እንደሚለግሱ የተመለከተ ማውጫ እና ተጨማሪ ፍንጮችን alexandriava.gov/FoodWaste**ን በመጎብኘት ይወቁ።**

ECO-CITY ALEXANDRIA

# የቆሻሻ ማስወገድ አገልግሎት

እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻን እና የግቢ ውስጥ ቆሻሻን ከለዩ በኋላ የሚቀረው የቤተሰብዎ ቆሻሻ ነው። የአሌክሳንደሪያ ከተማ በየሳምንቱ ከ 20,200 ደንበኞች ቆሻሻ ይሰበስባል። የምንሰበስበው ቆሻሻ ወደ ሀይልነት ይቀየራል። የአሌክሳንደሪያ ከተማ ቆሻሻውን በ 5301 Eisenhower Avenue በሚገኘው በ COVANTA Energy's Alexandria/Arlington Waste-To-Energy Facility ይደፋል።

አገልግሎት መስጫው 21 ሜጋዋት ሀይል በማመንጨት ወደ 15,000 የሚጠጉ መኖሪያ ቤቶችን የሀይል ተጠቃሚ ለማድረግ በቀን 975 ቶን ደረቅ ቆሻሻን በማቃጠል ቆሻሻን ወደ ሀይልነት ይቀይራል። ከተማው መቀነስን፣ መልሶ መጠቀምን፣ ወደ ምርትነትና ወደ ማዳበሪያነት መቀየርን በመከተል ለሀይል ማመንጨት የዩ.ኤስ የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲን የቀሻሻ አያያዝ/አስተዳደር ተዋረድ ይከተላል።

## የቆሻሻ አዘገጃጀት



የቤተሰብዎ የቆሻሻ ከረጢቶች በከተማው በሚሰጠው የቆሻሻ ማስቀመጫ ኮንቴነር ውስጥ ተደርገው በተመደበልዎ የቆሻሻ ማስረከቢያ ቦታ መንገድ (ወይም ጎዳና) ዳር መቀመጥ አለባቸው።

## ትልቅ ቆሻሻ - በእያንዳንዱ የመሰብሰቢያ ቀን

ትላልቅ እቃዎችን በዓመቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ በቆሻሻ ማስረከቢያ ቀንዎ ከቆሻሻ መጣያ ኮንቴነርዎ አጠገብ ማስቀመጥ ይችላሉ። ትላልቅ የብረት ቁሶች በ Alex311 የአገልግሎት ጥያቄ ማቅረብን ይፈልጋሉ (በምግብ ማብሰያ እቃዎች ላይ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል)፤ ወይም የጸደይ ወቅት ይሁንም አይሁንም ትላልቅ ቁሶችን ለማስነሳት በሚፈልጉበት ጊዜ ውጭ ያስቀምጧቸው።




**20,200**

የአሌክሳንደሪያ ከተማ በእያንዳንዱ ሳምንት ወደ 20,200 ከሚጠጉ ደንበኞች ቆሻሻ ትሰበስባለች።

**በ FY22 ውስጥ**

ከማምረቻው 10,000 ቶን ብረታ ብረት እንደገና ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል።

**በቀን 975**

ቶን ቆሻሻ ወደ ሀይልነት ይቀየራል

**21**

ሜጋ ዋት ሀይል በማመንት ወደ 15,000 ለሚጠጉ መኖሪያ ቤቶች የኤሌክትሪክ ኃይል ይቀርባል።



# የቆሻሻ ማስወገድ አገልግሎት



COVANTA Alexandria/Arlington Waste-To-Energy Facility

## የአካባቢ ማሻሻያዎች መጠናቀቅ

የቨርጂኒያ የአካባቢ ጥራት መምሪያ/ Virginia Department of Environmental Quality በCOVANTA Alexandria/Arlington Waste-To-Energy አገልግሎት መስጫ ለአነስተኛ የNOx (LN®) ቴክኖሎጂ ተከላና ስራ ማስጀመር የመጨረሻ ፍቃድ ይሰጣል።

በ 2022 Covanta Alexandria Waste-to-Energy አገልግሎት መስጫ ተቋም ለእጅግ ዘመናዊ ብክለትን መቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂው ያቀዳቸውን ማሻሻያዎች ሰርቶ አጠናቋል። ዓላማው የናይትሮጂን አክሳይድ (NOx) ልቀቶችን በተጨማሪ በመቀነስ የአካባቢ ጥበቃን ማገዝ ነው።

አሁን የተጠናቀቀውን የራሱን የዝቅተኛ NOx (LN) ቴክኖሎጂ በመትከል የናይትሮጂን ልቀቶችን ወደ 50% በሚጠጋ መጠን እንዲቀንሱ አድርጓል። ጥረቱ በ Covanta Alexandria-Arlington የአገልግሎት ተቋም ውስጥ ለማካሄድ የታቀደው የብዙ ዓመታት ፕሮጀክት አካል ነው።

## የቆሻሻ ማስረከቢያ ማዕከል

የከተው የ Waste-To-Energy አገልግሎት መስጫ ለሁሉም የአሌክሳንደሪያ ከተማ ነዋሪዎች የሚቀርቡ የመኖሪያ ቤት የቆሻሻ መረከብ አገልግሎቶችን ያጠቃልላል። ነዋሪዎች ቆሻሻቸውን በሳምንት አንድ ጊዜ ማስረከብ ይችላሉ። የቆሻሻ፣ ቁርጥራጭ ወይም ብረት ጠቅላላ ክብደት በአንድ ጉብኝት ከ 500 lbs. መብለጥ የለበትም። ነዋሪዎች የፎቶ ማረጋገጫ በማሳየት ነዋሪነታቸውን አዝንዲያረጋግጡ ሊጠየቁ ይችላሉ። (ተቀባይነት የሌላቸው እቃዎች ቲቪዎችን፣ ጉቶዎችን፣ አለቶችን፣ ብናኞችን፣ አሸዋን፣ በግፊት የሚሰሩ ሲሊንደሮች/ታንከሮችን፣ የግንባታና የህንጻ ተረፈ ምርቶችን፣ አደገኛ ቆሻሻዎችን፣ ጥይት/ፈንጂዎችን፣ ቁጥጥር የሚደረግበት የብረት ቆሻሻን እና የራዲዮ አክቲቭ/የከርሰ ምድር እቃዎችን ያጠቃልላሉ)።

? ጥያቄዎች አሉዎ? ለ COVANTA በስልክ ቁጥር 703.370.7722 ይደውሉ።

5301 Eisenhower Ave.

ከሰኞ እስከ አርብ ከ 6:00 a.m. to 5:30 p.m. ሰዓት፣
እና ቅዳሜ ከ 6:00 a.m. to 11:30 p.m. ሰዓት።

$ ነጻ

alexandriava.gov/RefuseCollection



### የህንጻ እቃዎች፣ ቋጥኞችና ቆሻሻ

የመኖሪያ ቤቶች ፕሮጀክቶች እና የመሬት ማስዋብ ተረፈ ምርቶች፤ ለምሳሌ: ቆሻሻ፣ አለት እና ድንጋይ በከተማዋ የስብሰባ ፕሮግራሞች ተቀባይነት የላቸውም። የጠጠሮች፣ ጡቦች፣ የባኞ ቤት ተገጣሚዎች፣ የግርግዳ ተገጣሚዎችና የእርሻ ጣውላ የንግድ የመጫንና ማስወገድ አገልግሎቶች ይቀርባሉ።

እባክዎ እንደ የመብራት ተገጣሚዎች እና የማድ ቤት መደርደሪያ ያሉ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ እቃዎችን በልገሳ ስለመስጠት ያስቡ። የቆሻሻ፣ አለት እና ድንጋይ የመሬት ማስዋቢያ ኩባንያዎችን ያነጋግሩ። የሌሎች የአካባቢ የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ዝርዝር ለማግኘት እና የ MWCOG's Builder ን እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ መመሪያ ለማግኘት ድረገጻችንን alexandriava.gov/RefuseCollection ን ይጎብኙ።

# የቤት ውስጥ አደገኛ ቆሻሻዎችና (HHW) እና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች

የማህበረሰባችንን ደህንነት፣ የውሀችንን ንጽህናና የአየራችንን ንጹህነት ለመጠበቅ ሲባል አንዳንድ የቤት ውስጥ ምርቶችን በልዩ ሁኔታ ማስወገድ ያስፈልጋል። እነዚህ ምርቶች አደገኛ ኬሚካሎችና ከባድ ብረቶችን ይይዛሉ። ከተማው ለእነዚህ እቃዎች በሳምንት ሁለት ቀናት የሚሰራ ሰራተኞች የተመደቡለት የመረከቢያ ቦታ አዘጋጅቷል።




3224 Colvin St. (ልክ ከ Duke St. ቀጥሎ)

ሰኞ ከ 7:30 am እስከ 3:30 pm ሰዓት ክፍት ነው *(ከበዓል ቀናት በስተቀር)*
ማክሰኞ: ዝግ ነው
ረቡዕ: ዝግ ነው
ሐሙስ: ዝግ ነው
አርብ: ዝግ ነው
ቅዳሜ: ከ 7:30 am እስከ 3:30 pm ሰዓት ክፍት ነው *(ከበዓል ቀናት በስተቀር)*
እሁድ: ዝግ ነው

ነጻ


የቁሳቁሶችን የተሟላ ዝርዝር ለማግኘት alexandriava.gov/go/2703 ን ይጎብኙ።



የቤት ውስጥ የጽዳት ምርቶች




ፀረ ተባዮች



የኤሌክትሪክ እቃዎች ቆሻሻ




ፕሮፔን ታንከር



ቀለም፣ ፍንጣቂዎችና ሟሟዎች



ሜርኩሪ የሚይዙ እቃዎች
ያረጁ የሙቀት መለኪያዎች እና ቴርሞስታቶች የፍሎረሰንት አምፑሎች




መኪና ኬሚካሎች



የእጽዋት መድሀኒቶች እና የጓሮ ምርቶች

## ባትሪዎች

ባትሪዎች ዩኤስ ውስጥ ዋነኞቹ የመኪና ቃጠሎዎች መንስኤዎች ናቸው። ማንኛውንም አይነት እንደገና ቻርጅ የሚደረጉ ባትሪዎችን ቆሻሻ ወይም እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ መጣያ ውስጥ አይክተቱ። እነዚህን ወደ HHW ማዕከል ይዘው ይምጡ። መደበኛ አልካላይን ወደ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ሊገባ ይችላል።



ሁሉም እንደገና ቻርጅ የሚደረጉ እቃዎች (ምሳሌ: Li-Ion፣ Ni-MH፣ Ni-Cd፣ Ni-Zn)
ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚያገለግል ሊቲየም (ምሳሌ: ቁልፍ/ሳንቲም፣ AA፣ AAA፣ 9V፣ C፣ D፣ CR123A፣ CR2)
ቀላጭ አሲድ (የመኪና) እና የታሸገ ቀላጭ አሲድ



## ላቴክስ ቀለም



### ...እንዴት መወገድ አለበት?

በዘይት ከተቀላቀለ ቀለም በተቃራኒው ላቴክን ቀለም አደገኛ ቆሻሻ ካለመሆኑም በተጨማሪ ከመደበኛ ቆሻሻ ጋር አብሮ ሊወገድ ይችላል። ከባዱ ነገር ቀለሙን ከቆሻሻ መጫኛ መኪና ላይ ሳይንጠባጠብ ወደ Waste-to-Energy ፋብሪካ መውሰዱ ነው። ከማስወገድዎ በፊት ቀለም የሚመጥ ነገር፣ ኪቲ ቆሻሻ ወይም የተቆራረጠ ቆሻሻ ላይ በማድረግ ያወፍሩት። ከዚም ሊድ ያድርጉበትና በክሪያውን የፕላስቲክ ከረጢት ውስጥ በመክተት ያሽጉት። በፍጹም ቀለሙን የእጅ መታጠቢያ ላይ ወይም የፍሳሽ ማስተላለፊያ መስመር ውስጥ አይጨምሩ! የቀለም ቆሻሻን ስለመቀነስ የተመለከቱ ፍንጮችን **ገጽ 21 ላይ ይመልከቱ** ።



### ...የምግብ ዘይቶች፣ ቅባቶችና ግሪስ?

አነስተኛ መጠን ከሆኑ በወረቀት መጠቅለያዎች ተጠቅልለው በመደበኛ የቆሻሻ መጣያ ውስጥ ሊጣሉ ይችላሉ። መጠኑ መካከለኛ ከሆነ በቀላጭ የሚጠብቅ መክደኛ ባለው ኮንቴነር ውስጥ ተከተው በመደበኛ የቆሻሻ መጣያ ውስጥ ሊጣሉ ይችላሉ። መጠናቸው ከፍተኛ ከሆነ ዘይቱን ከውስጡ ዘይት ባልቀ የዘይት መያዣ ኮንቴነር ውስጥ ለማድረግ የሬስቶራንት ሥራ አስኪያጅን ፍቃድ ስለመጠየቅ ያስቡ። ዘይት፣ ቅባቶች ወይም ግሪሶችን በፍጹም የእጅ መታጠቢያ ላይ ወይም የፍሳሽ ማስተላለፊያ መስመር ውስጥ አይጨምሩ።



### ...የታዘዘ መድሀኒትስ?

መድሀኒቶችን ያለ አግባብ ሊጠቀሟቸው ከሚችሉ ሰዎች እጅ በማራቅ ከተማዋን ይርዱ እንዲሁም ንጹህ የመጠጥ ውሀ ምንጮቻችንን ካልተገቡ የመድሀኒት አወጋገዶች ነጻ ያድርጉ። በፍጹም መድሀኒት ወደ ሽንት ቤት ወይም ወደ ፍሳሽ ማስተላለፊያ መስመር አይክተቱ። የትኛውንም ያረጀ ወይም የማያስፈልግ መድሀኒትን አመቱን በሙሉ ለሚከተሉት ማስረከብ ይችላሉ:

- የ APD ዋና መ/ቤት (3600 Wheeler Ave.)
- በ Del Ray ውስጥ የሚገኘው የመንደር ውስጥ ፋርማሲ (2204 Mt. Vernon Ave.)
- ኢኖቫ አሌክሳንድሪያ ሆስፒታል/ Inova Alexandria Hospital (4320 Seminary Rd.)



### ...ስለት ነገሮች?

በቢሯቸው መርፌ ወይም "ስለት ነገሮች" ማስወገጃ ፕሮግራም ያላቸው ስለመሆኑ ከዶክተር፣ ክሊኒክ ወይም ሆስፒታል ያረጋግጡ። ያለበለዚያ መርፌዎችን፣ ላንሴቶችን እና ሌሎች የተበከሉ ስለት ነገሮችን በማንኛውም ቀዳዳን በሚቋቋሙ፣ ሊታሸጉ በሚችሉ፣ በሚጣሉ የቤት እቃዎች (ለምሳሌ: ባዶ ጠርሙስ፣ የልብስ ማጠቢያ ጠርሙስ ወይም የብረት ቡና ጣሳ) ውስጥ ይክተቱ። በእቃዎቹ መያዣ ላይ "ስለት ነገሮች" ብለው ይጻፉባቸው። አንዴ የእቃ ማስቀመጫ ኮንቴነርዎ ባገለገሉ መርፌዎች ከሞላ በኋላ የመያዣውን አንደኛውን ክፍል በማንጫና ሌላኛውን ክፍል በውሀ ይሙሉ። + ከዚያም ያገለገሉ ስለት ነገሮችን ለማከም ውህዱን ለ20 ደቂቃዎች ያክል ይዘፍዝፋት። ከዚያም ውህዱን ሲንክ ውስጥ ይጨምሩና የማስወገጃ ኮንቴነሩን ቆሻሻ መጣያ ላይ ከመጣልዎ በፊት ክዳኑን ያሽጉና በማጣበቂያ ያጣብቁ። ኮንቴነሩን በመደበኛ የቆሻሻ ማስቀመጫ ቅርጫትዎ ውስጥ ይጣሉት።



### ... ፈንጂዎች እና ጥይቶችስ?

ተቀጣጣይና ፈንጂ መሳሪያዎች በአቅራቢያ ወደሚገኝ የፈንጂ መሳሪዎች ማስረከቢያ ጣቢያ መወሰድ አለባቸው። ጥይቶች ወደ ፖሊስ መምሪያ መወሰድ አለባቸው። እባክዎ ማስረከቡን ለማመቻቸት በሚከተለው የአደጋ ያልሆነ ስልክ ቁጥራቸው ይደውሉላቸው (703.746.4444).

# ባትሪዎች





## ባትሪዎችን ደህንነትን በጠበቀ መልኩ ማስወገድ

እንዳገና ቻርጅ የሚደረጉ ባትሪዎች ያልተገባ አወጋገድ በቆሻሻ ኢንዱስትሪው ውስጥ ከዋና ዋና የመኪና ቃጠሎ መንስኤዎች ውስጥ አንዱ እንደሆነ ያውቃሉ?

እንደገና ቻርች የሚደረጉ ባትሪዎችን ወይም አንድ ጊዜ ብቻ ያገለገሉ የሊቲየም ባትሪዎችን እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ ወይም ቆሻሻ ቅርጫቶች ውስጥ አይጣሉ።

እንደገና ቻርጅ የሚደረጉ ባትሪዎችዎን (ለምሳሌ: Li-Ion፣ Ni-Cd፣ Ni-Mh፣ Ni-Zn)፣ አንድ ጊዜ ብቻ ያገለገሉ የሊቲየም ባትሪዎችዎን (ምሳሌ: ቁልፍ፣ የሳንቲም ሴል AA፣ AAA፣ 9V፣ C፣ D፣ CR123A፣ CR2) እና ከ 9 ቮልት በላይ የሆኑ ባትሪዎችዎን ደህንነቱ ለተጠበቀ አወጋገድ በተፈቀደው የማስወገጃ ቦታ በመጣል የሰራተኞቻችንን ደህንነት ለመጠበቅ ያግዙን።




**ማስታወሻ:** ሻልካላይን ባትሪዎች (ምሳሌ: AA፣ AAA ባትሪዎች) ደህንነትን በጠበቀ ሁኔታ የቆሻሻ መጣያ ላይ ሊወገዱ ይችላሉ።

## የመጣያ/ማስረከቢያ ቦታዎች




**የቤት ውስጥ አደገኛ ቆሻሻዎችና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች መሰብሰቢያ ማዕከል**

ቦታ: 3224 Colvin Street

ሰዓቶች:

ሰኞ ከ 7:30 am እስከ 3:30 pm ሰዓት ክፍት ነው *(ከበዓል ቀናት በስተቀር)*
ማክሰኞ: ዝግ ነው
ረቡዕ: ዝግ ነው
ሐሙስ: ዝግ ነው
አርብ: ዝግ ነው
ቅዳሜ: ከ 7:30 am እስከ 3:30 pm ሰዓት ክፍት ነው *(ከበዓል ቀናት በስተቀር)*
እሁድ: ዝግ ነው

ለተጨማሪ የቆሻሻ መጣያ ቦታዎች በከተማው ውስጥ በሚገኙ በጎ ፍቃደኛ ቸርቻሮ አቅራቢዎች ይቀርባሉ፤ እባክዎ alexandriava.gov/go/3619 ን ይጎብኙ።

## መጣል/መረከብ የሚችሉ ባትሪዎች ምሳሌዎች

እንደገና ቻርጅ የሚደረጉ ባትሪዎች እርስዎ ከሚያስቧቸው ቦታዎች የበለጠ በብዙ ቦታዎች ይገኛሉ።

- ገመድ አልባ የሀይል እቃዎች (ምሳሌ: በንፋስ ቅጠል መጥረጊያዎች፣ መሰርሰሪያዎች፣ መጋዞች፣ መፍጫዎች፣ የሳር ማጨጃዎች)
- የሞባይል ስልኮች፣ ገመድ አልባ ስልኮች፣ ባለ ሁለት መስመር ራዲዮዎች
- የመብራት ባትሪዎች
- ላፕቶፖችና ታብሌቶች
- የህክምና መሳሪያዎች
- የህጻናት አሻንጉሊቶች
- ሙዚቃ ያላቸው የሰላምታ መስጫ ካርዶች
- ቁልፍ አልባ የበር መቆጣጠሪያዎች፣ የርቀት መቆጣጠሪያዎች
- የኤሌክትሮኒክስ ሲጃራዎች
- የኤሌክትሪክ የጥርስ ቡርሾች
- ጭስ መመርመሪያዎች



Picture credit: Call2Recycle



# የመቀነሻና መልሶ መጠቀሚያ ፍንጮች








**ቆሻሻን መቀነስና መልሶ መጠቀም የተፈጥሮ ሀብትና አካባቢን ለመጠበቅ እና ወጪዎችን ለመቀነስ የሚያስችል እጅግ ውጤታማ መንገድ ነው።**

1. የማይፈልጓቸውን ልብሶች፣ አሻንጉሊቶችና የቤት ውስጥ እቃዎችን ይለግሱ ወይም ይሸጡ። የማስረከቢያ/መስጫ ቦታዎችን ለማወቅ የከተማውን እንደገና መጠቀሚያ ማውጫ በ alexandriava.gov/19202 ይጎብኙ።
2. ከክሬዲት ካርድ ልመናዎች እና ሌሎች የማይፈለጉ የፖስታ አይነቶች መርጠው ይውጡ። Visit catalogchoice.org.
3. ያልዎትን ምግብ በመጠቀም የምግብ እቅድዎን አስቀድመው በማዘጋጀት እና ምግብዎን ለረጅም ጊዜ ሳይበላሽ በማቆየት የምግብ ቆሻሻን ይከላከሉ። እንደ የመወያያ እራት ፓርቲ ማስያ፣ የምግብ ዝግጅት የገበያ ዝርዝር፣ መረጃ ሰጪ የምግብ ማከማቻ መመሪያ የመሳሰሉ መሳሪያዎችና ሌሎችንም ለማግኘት savethefood.comን ይጎብኙ።
4. የፕላስቲክ ከረጢቶችን ለመቀነስ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ከረጢቶችን ይግዙ።
5. ምሳዎን እንደገና ጥቅም ላይ በሚውል መያዣ ይያዙ እንዲሁም የመመገቢያ እቃዎችን ከቤትዎ ያምጡ።
6. አንድ ጊዜ ተጠቅሞ መጣልን ለመቀነስ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውል የውሀ ጠርርሙስ ወይም ኩባያ ይመልከቱ።
7. ስጦታዎችን በስጦታ እቃ መጠቅለያ ይጠቅልሉ።
8. እቃዎችን ከማስወገድዎ በፊት በማደስ ወይም በመጠገን የአገልግሎት ጊዜያቸውን ያርዝሙ።
9. **የቀለም ቆሻሻን ይቀንሱ:-** ለፕሮጀክትዎ ቀለም በሚገዙበት ወቅት ከሚያስፈልገው በላይ ቀለም መግዛትን ለማስቀረት የቀለም ስሌት መስሪያ ስለመጠቀም ያስቡ። ከመጠን በላይ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ቀለም የሚኖርዎት ከሆነ ይህን ስለመለገስ፣ ሊጠቀመው ለሚችል ሰው ስለመስጠት፣ ወይም ቀለሙን በ Colvin St. ወደሚገኘው የ HHW ማዕከል ስለመወሰድ ያስቡ።

# የፕላስቲክ ከረጢቶችን ይቀንሱ




## የፕላስቲክ ከረጢት ግብር

የአሌክሳንደሪያ ከተማ ከአርሊንግተን፣ ሎውንዳን እና የፌየርፋክስ ካውንቲዎች ጋር በመተባበር ከምግብ/መጠጥ መደብር፣ ፈጣን ምግብ መሸጫ እና የመድሀኒት መደብሮች በሚጣሉ የፕላስቲክ ከረጢቶች ላይ በከረጢት 5-ሳንቲም ግብር እንዲከፈል አጽድቀዋል። ግብሩ ከጥር 1፣ 2022 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ሆኗል።

## የኋላ ታሪክ

ክብደታቸው ቀላል የማይባሉ የፕላስቲክ ከረጢቶች በውሃ ቦይ ውስጥ እንደ ቆሻሻ በብዛት የሚገኙ ሆኖ እንደ በካይ ነገር ይቆጠራሉ። የዱር እንስሳት በአብዛኛው የፕላስቲክ ከረጢቶችን ምግብ ስለሚመስሏቸው የሚመገቧቸው ከመሆኑም በተጨማሪ የበሰበሰ ፕላስቲክ ጥቃቅን ቅንጣቶች ወደ ምግብ ውስጥ ይገባሉ። ከ 2017 ዓ.ም ጀምሮ፣ በሚከሄደው ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈው የከተማው የቆሻሻ ስማርት ስትራቴጂያዊ እቅድ እና የአካባቢ ጥበቃ የድርጊት መርሀግብር (EAP) ሂደት ላይ የአሌክሳንደሪያ ከተማ ነዋሪዎች የአሌክሳንድሪያ ከተማ ነዋሪዎች የፕላስቲክ ከረጢቶችን አነስተኛ የአካባቢ ተፅእኖ ከማየት አንጻር አንድ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉ የፕላስቲክ ከረጢቶች ላይ ስጋቶቻቸውን ገልጸዋል።

## ለነዋሪዎች የተሰጠ መረጃ

ከምግብና መጠጥ መደብሮች፣ ፈጣን ምግብ መሸጫ መደብሮችና የመድሀኒት መደብሮች በሚገዙበት ወቅት በሚገዙበት ጊዜ ሁሉ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ከረጢትዎን ይዘው በመሄድ 5-ሳንቲም የከረጢት ክፍያዎን ያስቀሩ።



ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ይጎብኙ:-
alexandriava.gov/go/2091

## ለ SNAP / WIC ማህበረሰብ ተደራሽ የሆነ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ከረጢት

ከተማው የፕላስቲክ ከረጢት ግብር በጥር 1፣ 2022 ዓ.ም ተፈጻሚ ከመሆኑ ቀደም ብሎ ለተጨማሪ ምግብ ድጋፍ ፕሮግራም (SNAP) እና የሴቶች፣ ጨቅላ ህጻናትና ህናት (WIC) ማህበረሰቦች እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ከረጢቶችን አድሏል።

## አቅርቦቶቹ እስከሚያልቁ ድረስ ተይዘው ለሚሄዱ እቃዎች እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ከረጢቶች ይቀርባሉ

### የማህበረሰብና የሰብአዊ አገልግሎቶች የፊት ጽህፈት ቤት (DCHS)

- 2525 Mount Vernon Ave.
- ከሰኞ-አርብ ከ 8:00 a.m. - 5:00 p.m. ሰዓት

### የትራንስፖርትና አካባቢ አገልግሎቶች መምሪያ (T&ES)

- 2900-B Business Center Dr.
- ከሰኞ-አርብ ከ 8:00 a.m. - 4:00 p.m. ሰዓት



# የምግብ ቆሻሻን መቀነሻ ስትራቴጂዎች

የምግብ ቆሻሻ ከምንጥለው ቆሻሻ ውስጥ 25% ያክሉን ድርሻ ይይዛል። ምግብን በጥሩ ሁኔታ በመያዝ እንደ ቆሻሻ እንዳይጣል ለመከላከል የሚከተሉትን ቀላል ፍንጮች ይከተሉ።



### ስማርት ገበያ

የሚፈልጉትን ብቻ ይግዙ በተለይም የማድ ቤት ምግቦችን መጀመሪያ ይግዙ። በዚህ ሳምንት ለቤተሰብዎ ምን ያክል ምግብ እንደሚበቃው እና ለሚቀጥለው ግዢ እስከሚሄዱ ምን ያክል ጊዜ እንደሚያስፈልግዎ ያስቡ።



### ስማርት ዝግጅት

በቀላሉ የሚበላሹ ምግቦችን እንደገዙ ወዲያውኑ ያዘጋጁ። ጊዜን፣ ጥረትን እና ገንዘብን በመቆጠብ በሳምንቱ ውስጥ ምግቦችን ማሸት ቀላል ዘዴ ነው።



### ስማርት ማስቀመጫ

የትኞቹ ፍራፍሬዎችና አትክልት ፍሪጅ ውስጥ ወይም ከፍሪጅ ውጭ ለረጅም ጊዜ እንደሚቆዩ ይወቁ። ሳይበላሹ መወመጥ እስከሚችሉበት ከፍተኛ ጊዜ በማስቀመጥ የተሻለ ጥፍጥና ይኖራቸዋል እንዲሁም ለረጅም ጊዜ ለምግብነት ያገለግላሉ።



### ስማርት ቁጠባዎች

የገዙትን ነገር ይብሉ። የተረፉ እና የቆዩ የምግብ ግብዓቶችን ልብ ይበሉ። ቤተሰቦች የምግብ መበላሸትን ለመከላከል በፍሪጃቸው ውስጥ ቀደም ብለው ለሚበሉ ምግቦች የራሳቸው የሆነ ቦታ እንዲያዘጋጁ እና መመሪያውን እንደ ስእላዊ ማስታወሻ እንዲለጥፉ ይበረታታሉ።

alexandriava.gov/go/4260

# የበዓል ቆሻሻን መቀነስ

ከምስጋና ስጦታ መሰጣጫ ቀን አንስቶ እስከ አዲስ ዓመት ድረስ ከቤት የሚወጡ ቆሻሻዎች በአማካኝ በ 25% ይጨምራሉ። እነዚህን ቀላል ፍንጮች በመጠቀም የበዓል ወቅት ቆሻሻን በመቀነስ ያግዙ።



### ጥልፍልፍ ነገሮችን ሰማያዊው የቆሻሻ ቅርጫት ውስጥ አይክተቱ

በዚህ የበዓል ወቅት ጥልፍልፍ ቁሳቁሶችን እንደገና ጥቅም ላይ በሚውል ቆሻሻ ቅርጫት ውስጥ አለመክተትን አይርሱ። ሪባንን እና ቀስቶችን እንደገና ይጠቀሙ ወይም በቆሻሻ መጣያ ውስጥ ያስቀምጧቸው።



### ባዶ፣ ዝርግ፣ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ የመጫኛ ሳጥኖች

በዚህ የበዓል ወቅት የመጫኛና የስጦታ መስጫ ሳጥንዎን ባዶ፣ ዝርግ ማድረግና እንደገና ጥቅም ላይ ማዋልን አይርሱ። ሳጥኖችን ዝርግ ማድረግ እንደገና ጥቅም ላይ በሚውል ቆሻሻ ቅርጫትዎ ውስጥ ተጨማሪ ቦታ ይፈጥራል።



### ምግብ በሚያዘጋጁበት ወቅት እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል

በዚህ የበዓል ወቅት ምግብ ያበስላሉ? እንደ የወተት ካርቶኖች፣ የአልሙኒየም ድስቶችና የዳቦ መጠቅለያዎች የመሳሰሉ ቁሳቁሶች እንደገና ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ያውቁ ነበር። እነዚህ ቁሳቁሶችን የቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ውስጥ ከመጨመርዎ በፊት አጥበው ማድረቅዎን ያረጋግጡ።

እንደገና ጥቅም
**ላይ የማዋያ**
ወቅት ነው

| | መልሶ መጠቀም | እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል | ቆሻሻ |
|---|---|---|---|
| አንጸባራቂ | ❄ | ❄ | |
| የብረት | ❄ | | ❄ |
| ሰም የተቀባ | ❄ | | ❄ |
| ጠፍጣፋ | ❄ | ❄ | |
| የሸንት ቤት ወረቀት | ❄ | | ❄ |
| ጥቅል ካርቶን | ❄ | ❄ | |
| ካርቶን | ❄ | ❄ | |




### ከዕቃዎች ይልቅ ልምዶችን ያጋሩ!

የትዕይንት ቲኬቶች፣ የጥንዶች እራት ወይም የፊልም መግቢያ ኩፖኖች ሁሉም ምንም ማሸጊያ የማይጠይቁ ጥሩ ስጦታዎች ናቸው። በነ አድራሳት ተቋማትን በተለይም በወረርሽኙ የተጎዱ ተቋማትን ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል አማራጭ ስጦታ ይስጡ። ማስታወሻ ከነገሮች በላይ ለረጅም ጊዜ እየታወሰ እንደሚቆይ ልብ ይበሉ።



### ስጦታን መልሶ ጥቅም ላይ በሚውል እና/ወይም እንደገና ጥቅም ላይ በሚውል ቆሻሻ ኮንቴነሮች ውስጥ ይጨምሩ።

በዚህ የበዓል ወቅት የፈጠራ ችሎታ አይለይዎ! ከኦንላይን ግዢዎች የሚገኙ ሳጥኖችን እንደ ስጦታ መስጫ ሳጥኖች ይጠቀሙ። ወይም አሁን ያሉዎትን ቁሳቁሶች እንደ ሁለተኛ የስጦታ መጠቅለያ ይጠቀሙ። እነዚህ ጋዜጦችን፣ መጽሄቶችን እና ከረጢቶችን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ። ጠቃሚ ምክር:- "አዝናኝ ወረቀቶች" ወይም አስቂኝ ነገሮች ለህጻናት አዝናኝ ስጦታዎች ናቸው።



### ለበዓል ማስዋቢያዎ የተፈጥሮ ቁሳቁሶችን ይጠቀሙ

እውነተኛ አረንጓዴ ነገሮችን በመጠቀም ያስውቡ። የተፈጥሮ የአበባ ጉንጉኖች እና የአበባ ጉንጉኖች ከበዓል በኋላ ከሌላው ከቤት ውስጥ ቆሻሻዎ ጋር ሊበሰብሱ ይችላሉ። ማንኛውንም ሽቦዎች፣ መብራቶችና ሪባኖችን ማንሳትዎን ያረጋግጡ። የግቢ ውስጥ ቆሻሻን እንደገና ጥቅም ላይ ስለማዋል በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የግቢ ውስጥ ቆሻሻን እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል ገጽን ይመልከቱ።

## የመጠቅለያ ወረቀት መመሪያ

የግዢ እቃዎች መጠቅለያ ወረቀት የሚሰራው እንደገና ጥቅም ላይ ከሚውሉ በተጨማሪው ወደ ሶፍትነትና እንደገና ወደ መጠቅለያ ወረቀትን ሊቀየሩ ከሚችሉ ቁሳቁሶች ነው። ያስታውሱ: የብረት/አንጸባራቂ የወረቀት መጠቅለያ እንደገና ጥቅም ላይ አይውልም።

alexandriava.gov/go/4151



# ለመቀነስ፣ መልሶ ለመጠቀም እና እንደገና ለመጠቀም የሚረዱ መሳሪያዎች

### አንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ዕቃዎችን የመለየት ጌም/ RECYCLE RIGHT SORTING GAME

ከተማው እርስዎን እንዴት ወደ ምርትነት የሚቀየሩ፣ የጓሮ ቆሻሻና ቆሻሻን በአግባቡ እንደሚለዩ የሚያስተምር የመለያ ጌም ተግባራዊ አድርጋለች። የከተመዋን አገልግሎቶች በመጠቀም የመለየት እውቀትዎን ይፈትኑ እና የራስዎን የዲጂታል አሌክሳንደሪያ ፓርክ ይገንቡ።

alexandriava.recycle.game




### ምን ወዴት ይሄዳል?

የትኞቹ እቃዎች እንደገና እንደሚቀየሩ ወይም በቆሻሻነት እንደሚጣሉ እርግጠኛ ያልሆኑበት ጊዜ አለ? በከተማው አዲስ "ምን ወዴት ይሄዳል?" መሳሪያ አማካኝነት ይገምቱ። በቀላሉ ጥያቄ የፈጠረብዎትን እቃ ስም ይጻፉ እና ይህን እቃ እንዴት በተሻለ መልኩ በከተማዋ ውስጥ እንደሚያስወግዱ የተመለከተ መረጃ ይመጣልዎታል።

alexandriava.gov/Recycling




### የመልሶ መጠቀም ማውጫ

መቀነስና መልሶ መጠቀም ፈልገው ሆኖም ከምን መጀመር እንዳለብዎ አላወቁም? አዲስ የመልሶ መጠቀሚያ ማውጫ ለማግኘት የከተማውን ድረገጽ ይጎብኙ! መጠገን፣ መለገስ እና እንዳገለገለ ምርት መሸጥ የሚችሉባቸውን የአካባቢ ምንጮች ዝርዝር ያግኙ።

alexandriava.gov/go/2773




# የሚያግዙ መሳሪያዎች
# እንደገና መሙላትና ያለ ማሸጊያ ይዞ መሄድ

## ማሸጊያ የማይፈልጉ እቃዎች ካርታ

ቆሻሻን ስለመቀነስ ወይም ያለ ማሸጊያ ይዘው ስለመሄድ ለማወቅ ጓጉተው ያውቃሉ? ከማሸጊያ ነጻ እቃዎችን ስለመግዛት እና የቤት ውስጥ ማሸጊያዎችዎንና የፕላስቲክ ቆሻሻን ስለመቀነስ በተመለከተ ጥቂት ቀላል ፍንጮችን ለማወቅ ድረገጻችንን ይጎብኙ።

alexandriava.gov/go/2773



## የምግብ ቆሻሻን ይከላከሉ

በብልሀት የመግዛት፣ ያልዎትን ምግብ የመጠቀም እና ምግቦችን ለረጅም ጊዜ ሳይበላሹ የማቆየት ፍንጮችን በመጠቀም የምግብ ቆሻሻን ይከላከሉ። እንደ መረጃ ሰጪ የእራት ፓርቲ ስሌት መስሪያ፣ ከቀጣዩ የግዢ ዝርዝር እስከ ምግብ ዝግጅት ለማዘጋጀት የሚረዳዎ የዲጂታል መሳሪያ፣ መረጃ ሰጪ የአቀማመጥ መመሪያ የመሳሰሉ መሳሪያዎችን እና ሌሎችንም ለማግኘት የ Save the Food ድረገጽን ይመልከቱ።

alexandriava.gov/FoodWaste



# እኛን እንዴት እንደሚያነጋግሩን

Alex311 ከ 175 በላይ የከተማው አገልግሎቶች ጋር በተለያዩ አመቺ መንገዶች ያገናኝዎታል። የ Alex311 የሞባይል መተግበሪያና ድረገጽ ፎቶዎችን እንዲጭኑ እና የአገልግሎቶች መጠየቂያ ቦታን እንዲገልጹ ያስችልዎታል። አሌክሳንደሪያ ውስጥ ከየትኛውም ቦታ ሆነው ወደ 311 ወይም 703.746.4311 ይደውሉ፣ ወይም ጥያቄዎችን በፌስቡክ፣ ትዊተር እና በአካል ያቅርቡ። የአገልግሎት ጥያቄ በሚቀርብበት ወቅት የዝርዝሮች ማጠቃለያን፣ እንደ ጥያቄው አይነት ላይ ተመስርቶ የሚጠበቀው የምላሽ መስጫ ቀንን እና የሂደት መከታተያ የጉዳይ ቁጥርን ጨምሮ የያዘ ኢሜይል ይደርስዎታል።



ALEX 311

እርስዎን ከከተማው አገልግሎቶች ጋር ያገናኝዎታል

alexandriava.gov/Alex311

## ግንኙነት ማድረግዎን ይቀጥሉ

የከተማውን ድረገጽ
በ alexandriava.gov
ይጎብኙ

የሀብት ማስመለሻ
ክፍልን ድረገጽ በ
alexandriava.gov/
ResourceRecovery ይጎብኙ።

በማህበራዊ ትስስር ገጽ ይከተሉን
@AlexandriaVATES

## የበዓል የጊዜ ሰሌዳ/መርሀግብር

ለበዓል የሥራ የጊዜ ሰሌዳ፣ እባክዎ alexandriava.gov/ResourceRecovery ይጎብኙ

የአሌክሳንድሪያ ከተማ
301 KING STREET
ALEXANDRIA, VA 22314

Presort Standard
US Postage
PAID
Permit # 2782
Merrifield, VA

የአሌክሳንድሪያ ከተማ
የመጓጓዣ እና የአካባቢ አገልግሎቶች
ሀብትን መልሶ ማግኛ ክፍል

alexandriava.gov/TES

@AlexandriaVATES

@AlexandriaVATES

@AlexandriaVATES

ECO-CITY ALEXANDRIA

Alexandria City Hall 301 King Street Alexandria, VA 22314